


Source: Abugeda Website - http://www.abugidainfo.com/amharic/index.php/13345

# ትግልሽን አደነቅሁ

አንቀልባ እንኳን የለሽ

ልጅሽን ለመሸከም፣

ነጠላሽም አጭር

ጠርፎ የያዘው

የልጅሽን እግሮች

ችግር አልገታሽም፤

ለመብትሽ ለመቆም።

ማን ልበል እህቴ፣

ግምባርሽን ለጸሃይ

ተከሻሽን ለሸክም፣

ካስፈለገም ደግሞ

ደረትሽን ለጨካኝ

ብለሽ መነሳትሽን፣

ስሚትሽ ሲናገር

ልጅሽም መሰከረ፣

አፉ እንኳ ባይፈታ

በነጠላ ጋርዶ

ጀርባሽን ተማምኖ፣

ማን አለብኝ ብሎ

ማንም ባይጠይቀው፤

ነግ  የሱ ነጻነት መሆን ስለገባው።

ማን ልበል እህቴ፣

ደከመኝ ሳትይ

ልጅሽን አንግበሽ፣

ጸሐዩ ሲያቃጥልሽ፣

እውቃ እንካን ሳይኖርሽ፣

ትግልሽን አደነቅሁ

በቃም በማለትሽ፤

አፉን ለማዘጋት

አለምነው መኮነን፣

አንዲያ እንኳን ቢያዋረድሽ።

**ማን ልበል እህቴ**

**እጅግ አደነቅሁሽ!**

ሰላም ላንች ይሁን

በነፃነት ኑሪ እንኳን ስድብና

ኀሣም ሳይበግርሽ፤

በኢትዮጵያ አገርሽ

የ ኢያቶችሽ ደም ነው

**<u>ማንነትሽን አስምሮ አገር ያቆየልሽ።</u>**

**ማን ልበል እህቴ**

**እኔስ አደነቅሁሽ፤**

**በቃ በማለትሽ።**

አለምነው መኮነን

አፉ አንዳመጣ የሚሳደበውን፣

ሃፍረትም ያዘለውን፣

አዳምጬኝ እባክሽ ይቅር እንበለው፤

**አረ ስምሽ ማን ነው?**

ቆርጠሽ መነሳትሽን

ፊትሽ የሚያሳየው

እህቴ ንገሪኝ **አረ ስምሽ ማነው** ?

**ሆኖም አደነቅሁሽ፤**

**በቃ በማለትሽ።**

© ለምለም ፀጋው ልጇን አዝላ ለሙብቷ ለምትቃትተው

እህት በባሕር ዳር ከተማ ለአክብሮት የተጻፈ፣ February 23, 2014